**ውሣኔ፡** - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የጉምሩክ ባለስልጣን በህጉ መሠረት ከጉምሩክ መጋዘን እንዳይወጣ ላደረገው እዳ ያስከፈለውን የመጋዘን ኪራይ የሚመለስበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡
2. የጉምሩክ ባለሥልጣን ዴክላራሲዮን መስጠት የሚችለው በህጉ መሠረት የጉምሩክ ስነ ስርአት ለተፈጸመበት እቃ ብቻ ነው፡፡ የጉምሩክ ስነ ስርአት ላልተፈጸመበት እቃ ዴክላራሲዮን ባለመስጠቱ በእቃው ባለቤት ለሚደርስ ጉዳት የጉምሩክ ባለስልጣን አይጠየቅም፡፡



የሰበር መ/ቁ. 17533

ጥቅምት 18 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጐስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡** - የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ኃ/መለኮት አበበ ቀርቧል፡፡

**መልስ ሰጪ፡** - አቶ ሙሉ አብርሃ ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ***ፍ ር ድ***

ይህ መዝገብ ተከፍቶ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኑ አመልካች ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ ጉዳዮን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተመሣሣይ መንገድ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት

መሆኑን በመግለጽ ጥቅምጽ 29 ቀን 1997 ዓ.ም ተጽፎ እንዲቀርብ ባደረገው አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

በአሁኑ ተጠሪ ከሣሽነት የተጀመረውን ክርክር በመጀመሪያው በፍ/መ/ቁ.34187 ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ ከውጭ አገር በሕጋዊ መንገድ በማስመጣት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባሁትን 1600 ካርቶን የፎቶ ኮፒ ወረቀት ተከሣሹ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ያለአግባብ ይዞ በማቆየት ለመጋዘን ኪራይ ያስከፈለኝ ብር 11.793.10በ ተመላሽ እንዲያደርግልኝ፣ ተከሣሽ በመጨረሻ እቃውን ሲለቅ አብሮ መስጠት የሚገባውን ዲክላራሲዮን ለመስጠት ፈቃደኛ ሣይሆን በመቅረቱና በዚሁ ምክንያት እቃውን በሀገር ውስጥ ለገበያ በማቅረብ ለመሸጥ ባለመቻሌ ለመጋዘን ኪራይ ያወጣሁትን ብር 96.600 እንዲከፍለኝ፣ የእቃውን ዲክላራሲዮንም እንዲሰጠኝ በሚል ባቀረበው ክስ ላይ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን መልስ እንዲሰጥበት አድርጐ ካከራከረ በኋላ ሰኔ 14 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት መርምሮ በሰጠው ውሣኔ ተከሣሹ ከጉምሩክ ሕግ ጋር በተያያዘ ያነሣቸውን ክርክሮች ውድቅ በማድረግ ክስ የቀረበበትን



ገንዘብ ብር 112.069.95 ከሕጋዊ ወለድ እና ክርክሩ ካስከተላቸው ልዩ ልዩ ወጪዎች ጭምር ለከሣሹ እንዲከፍል፣ የእቃውን ዲክላራሲዮንም ተከሣሹ እንዲበትን ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ.32978 የይግባኝ አቤቱታ ሊያቀርብ የቻለ ቢሆንም ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም. በሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.337 መሠረት ይግባኙን ሠርዞበታል፡፡

ቀጥሎም በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አመልካች የአሁን ተጠሪ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት የከፈለው ኪራይ በሕጉ ሊመለስለት አይችልም፡፡ የጉምሩክ ባለሥልጣን እቃው በመጋዘን ለሚቆይበት ጊዜ ኪራይ የማስከፈል ስልጣን አለው፡፡ እቃው ተይዞ ሊቆይ የቻለው በቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት ላይ አንድ ካርቶን የያዘው አንድ ፓኬት የፎቶ ኮፒ ወረቀት ነው ተብሎ ቢገለጽም ሲፈተሽ አንዱ ካርቶን 5 ፓኬት የያዘ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ ተጠሪው ከውጭ አገር ያስመጣው 1600 ካርቶን በአጠቃላይ 6400 ተጨማሪ ፓኬቶች የያዘ መሆኑ በተደረገው ፍተሻና ምርመራ ስለተረጋገጠ እቃውን

የመያዝ ሥልጣን አለው። በእቃው ላይ ተገቢው ቀረጥ ሣይከፈልበት አመልካች ዲክላራሲዮን ለመስጠት አይገደድም። ተጠሪው እቃውን ከተረከበ በኂላ ለመጋዘን ኪራይ ከፍያለው የሚለውን ገንዘብ የምከፍልበት ምክንያት የለም ባይ መሆኑን በጽሁፍ እንዲቀርብ ያደረገው ማመልከቻ ያስረዳል።

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ነው ተብሎ በአመልካች በኩል የቀረበው ማመልከቻ ለተጠሪው እንዲደርሰው ተደርጐ የካቲት 7 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል። በተጠሪው በኩል የቀረበው ክርክር፡ -

ተጠሪ የእቃውን መጠንና ብዛት በተመለከተ የሰጠው መግለጫ ትክክለኛ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር በአሁኑ አመልካች የተካደ ፍሬ ነገር ስላልሆነ ለሰበር ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪው ስለዕቃው ብዛት አሳስቶ አቅርቧል በሚል የገለፀው ተቀባይነት የለውም። የቅድመ ጭነት ምርመራ እንዲያደርግ ኃላፊነትና ሥልጣን የተሰጠው ኤስ.ጂ.ኤስ ኩባንያ ሪፖርት ሲያደርግ በዕቃው ብዛትም ሆነ ክብደት ረገድ ስህተት በማድረግ በቀረጥና ታክስ ታሪፍ አመዳደብ ላይ በመንግሥት ገቢና



ጥቅም ላይ ላስከተለው ጉዳትም ሆነ ጥፋት ራሱ ኩባንያው ኃላፊነት ወስዶ ሊከፍል የሚገባው እንጂ እቃ አስመጪው የሚጠየቅበት ምክንያት የለም። ተጠሪው የፈፀመው ጥፋትም ሆነ ስህተት እንደሌለ ታምኗል። አመልካችም በተጠሪው በኩል የተፈፀመ ጥፋት እንደሌለ እያወቀ እቃው በጉምሩክ መጋዘን እንዲራገፍ በማድረግ ሲጠየቅ ባለማስረከብ በመጋዘን እንዲቆይ ያደረገው ያለአግባብ ነው። ዲክላራሲዮኑንም የመስጠት ግዴታ አለበት የሚል ይዘት ያለው ሲሆን አመልካች በበኩሉ በተጠሪው በኩል የተሰጠው መልስ ተቀባይነት የለውም የሚልባቸውን ምክንየቶች በመግለጽ ተከራክሯል።

ይህ ችሎት በበኩሉ በዚህ መዝገብ የቀረበውን ጉዳይ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል።

በዚህም መሠረት በተያዘው ጉዳይ ከሕጉ አኳያ ሊመረመሩ የሚገባቸውን የክርክር ነጥቦች፡ -

1ኛ/ እቃ አስመጪው ከውጭ አገር ወደ አገር ያስገባው እቃ በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ እንዲከፍል የተደረገው ኪራይ

ይመለስልኝ ብሎ የሚጠይቅበት የሕግ ምክንያት አለ ወይንስ የለም? የጉምሩክ ባለሥልጣንስ እቃው በመጋዘን ለቆየበት ጊዜ ያስከፈለውን ኪራይ ሊመልስ ይገባል የሚባልበት ምክንያት ይኖራል?

2ኛ/ የጉምሩክ ባለሥልጣን እቃ አስመጪው ከውጭ አገር ወደ አገር ያስገባው እቃ ብዛት በቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት ላይ ተገልጾ ከቀረበው መጠን በላይ በሚል እና ከቀረጥና ታክስ ጋር በተያያዘ ምክንያት ዲክላራሲዮን አልሰጥም ብሎ መከልከል ይችላል አይችልም?

3ኛ/ የአሁኑ ተጠሪ እቃውን ከተረከብኩ በኂላ ዲክላራሲዮን ባለማግኘቴ የተነሣ ሊሸጥ ባለመቻሉ ሌላ መጋዘን ተከራይቼ ለማቆየት አውጥቻለሁ የሚለውን ገንዘብ



የጉምሩክ ባለሥልጣን ለመክፈል ይገደዳል አይገደድም? የሚሉት መሆናቸውን ከመዝገቡ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በቅድሚያ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ ተከፍሏል የተባለው ኪራይ ሊመለስ ይገባል አይገባም የሚለው ክርክር ሲመረመር ከሣሽ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ከውጭ አገር ወደ አገር ያስገባው 1600 ካርቶን የፎቶ ኮፒ ወረቀት በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ በባለሥልጣኑ እንዲከፍል የተጠየቀውን ኪራይ ብር 11,793.10 ከፍሎ እቃውን በመረከብ ወስዶ ከቆየ በኂላ ይህንኑ ገንዘብ ሊመልስልኝ ይገባል ብሎ ሊከሰው የቻለው እቃው ወደ አገር እንደገባ እንዲያስረክብ ሲጠየቅ የዕቃው ብዛት በቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት ላይ ተገልጾ ከቀረበው በላይ ሆኖ ተገኝቷል በሚል ሣቢያ እቃውን ይዞ በመጋዘን በማራገፍ እንዲቆይ ያደረገው ያለአግባብ ነው በሚል ምክንያት መሆኑን የክሱ ፍሬ ነገር ያስረዳል፡፡

በሕጉ በኩል ያለው ሲታይ የጉምሩክ ባለሥልጣንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 43/ሀ/ ላይ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገባ እቃ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተፈጽሞበት እስኪወጣ ድረስ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ ኪራይ የሚከፈልበት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ኪራዩም የሚከፈለው ለባለመጋዘኑ የጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በዚሁ ሕግ መሠረት እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ ኪራይ መክፈል የሚገባው መሆኑን አውቆ የተጠየቀውን ኪራይ ከፍሎ እቃውን አውጥቷል፡፡ ተጠሪው የጉምሩክ ባለሥልጣን እቃውን በመጋዘን ያቆየው ያለአግባብ ነው በሚል የሚያቀርበውን የክርክር ምክንያት በተመለከተም የጉምሩክ ባለሥልጣን ተጠሪው ወደ አገር ያስመጣው 1600 ካርቶን የፎቶ ኮፒ ወረቀት በቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት ላይ እያንዳንዱ ካርቶን በውስጡ አንድ ፓኬት እንደያዘ ተደርጐ የቀረበለት ቢሆንም ሲፈተሽ እያንዳንዱ ካርቶን 5 ፓኬት የያዘ መሆኑን ሊያረጋግጥ በመቻሉ በሕጉ መሠረት ሊከፈልበት



ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በተያያዘ ምክንያት ይዞ ያቆየ ሆኖ የሚታይ እንጂ ከሕጉ ውጪ ፈጽሟል የሚባል ነገር የለም፡፡ የእጥፍ እጥፍ ሆኖ የተገኘው እቃ በህገወጥ መንገድ የገባ ነው ተብሎ ባይታይ እንኳን የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ሣይፈጽምበት ከጉምሩክ መጋዘን ሊወጣ አይችልም፡፡ ተጠሪው ይኸው የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ሣይፈፀም የጉምሩክ ባለሥልጣን ወዲያው እቃውን እንዲያስረክብ ሲጠየቅ ማስረከብ ነበረበት፣ በጉምሩክ መጋዘንም ማቆየት አልነበረበትም በማለት የማያቀርበው ክርክር በሕግ ተቀባይነት የለውም፡፡ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ የከፈለው ኪራይ ይመለስልኝ ብሎ የሚጠይቅበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕጉ መሠረት የተከፈለውን የመጋዘን ኪራይ የሚመልስበት ምክንያት የለም፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለእቃው ብዛት የተሣሣተ መረጃ የሰጠው የቅድመ ጭነት ምርመራ አድራጊው ኤል.ጂ.ኤስ የተባለው ኩባንያ ስለሆነ አቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ የተከፈለው የኪራይ

ገንዘብ ሊመለስለት ይገባል በሚል የወሰነው የጉምሩክ ሕግን ያገናዘበ አይደለም፡፡

የጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን ለመስጠት ይገደዳል አይገደድም የሚለውን ጭብጥ በተመለተም የአሁኑ አመልካች እቃውን የሚመለከት ዲክላራሲዮን ለሰጠው አይገባም በማለት አጥብቆ የሚከራከረው በእቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥ ተሟልቶ ሣይከፈል ዲክላራሲዮን ሊሰጠው አይችልም በሚል ምክንያት ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ቀረጡ ተሟልቶ ባይከፈልም የጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን አልሰጥም ብሎ ሊከለከል አይችልም፣ በእቃው ብዛት አገላለጽ ላይ ስህተት የፈፀመው የቅድመ ጭነት ምርመራ ያደረገው ኤስ.ጂ.ኤስ የተባለው ኩባንያ በመሆኑ በቀረጥና ታክስ ጉዳይ በኃላፊነት መጠየቅ ያለበት ይኸው ድርጅት ነው ባይ ነው፡፡

በተጠቀሰው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 2/18/ ላይ እንደተመለከተው “የጉምሩክ ዲክላራሲዮን” ማለት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ፣ ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ወይም



ተላላፊ እቃዎች ዝርዝር የሚገለጽበትና የጉምሩክ ሥነ ሥርአት የሚፈፀምበት በባለሥልጣኑ የሚዘጋጅ ቅጽ ሲሆን ከዚህ የሕግ አገላለጽ ዲክላራሲዮን በዋናነት የጉምሩክ ሥነ ሥርአት የሚፈፀምበት ሰነድ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት መፈፀም የሚለውም ሲታይ በቀረጥና ታክስ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የጉምሩክ ባለሥልጣንም ዲክላራሲዮን አዘጋጅቶ ሊሰጥ የሚችለው በሕጉ መሠረት ተገቢው ቀረጥና ታክስ እንዲከፈልበት ተደርጐ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ለፈፀመበት እቃ ነው፡፡ በሕጉ አግባብ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ላልተፈፀመበት እቃ ግን የጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን እንዲሰጥ ሕጉ አይፈቅድም፡፡ እቃ አስመጪው በበኩሉ ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገባ የተፈቀደለትን እቃ አይነት፣ ብዛትና ክብደት በትክክል ገልጾ ለባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በማቅረብ በታሪፍ መሠረት ተወስኖ የማጠየቀውን ቀረጥና ታክስ በመክፈል የጉምሩክ ሥነ ሥርአት እንዲፈፀምበት ላላደረገው እቃ ዲክላራሲዮን ይሰጠኝ ብሎ የመጠየቅ መብት ሊኖረው

አይችልም፡፡ በቀረበው ጉዳይ ደግሞ የአሁኑ ተጠሪ ከውጭ አገር ወደ አገር ባስገባው እቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ ተሟልቶ ያልተከፈለ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ በቅድመ ጭነት ምርመራው ሪፖርት ላይ የአሁኑ ተጠሪ ከውጭ አገር ወደ አገር የሚያስገባው 1600 ካርቶን የፎቶ ኮፒ ወረቀት እያንዳንዱ ካርቶን አንድ ፓኬት የፎቶ ኮፒ ወረቀት የያዘ መሆኑ ተገልጾ ለጉምሩክ ባለሥልጣን የተላከ ቢሆንም ወደ አገር ውስጥ ከገባ በኂላ ሲፈተሽ አንዱ ካርቶን አምስት ፓኬት የያዘ ሆኖ መገኘቱም ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪው ይህንኑ እያመነና በክርክሩም ሂደት በልዩነቱ ላይ ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ ብር 49.024.78 መኖሩን እየገለጸ ስህተቱን የፈፀመው የቅድመ ጭነት ምርመራ ያደረገው ኤስ.ጂ.ኤስ የተባለው ኩባንያ ስለሆነ ቀረጥና ታክስ ተሟልቶ ባይከፈልም የጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን ሊሰጠኝ ይገባል በሚል ያቀረበው ክርክር በሕጉ ተቀባይነት የለውም፡፡ የአሁኑ አመልካች የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ላልተፈፀመበት እቃ ለተጠሪው ዲክላራሲዮን መስጠት



አለበት በሚል የተሰጠው ውሣኔም ሕጉን መሠረት የደረገ ስላልሆነ የሚሰረዝ ነው፡፡

በመጨረሻም የአሁኑ ተጠሪ እቃውን ከተረከበ በኂላ ዲክላራሲዮን ባለማግኘቱ ምክንያት መጋዘን ተከራይቶ እቃውን ለማቆየት አወጣሁ የሚለውን ገንዘብ አመልካች ለመክፈል ይገደዳል አይገደድም የሚለው ሲመረመር ከላይ እንደተገለጸው የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕጉ መሠረት የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተሟልቶ ላልተፈፀመበት እቃ ዲክላራሲዮን ለመስጠት የማይገደድ ሆኖ ስለተገኘ አስመጪው እቃውን ካስወጣ በኂላ ዲክላራሲዮን ባለማግኘቴ ምክንያት ለመጋዘን ኪራይ አውጥቻለሁ የሚለውን ብር 96,600 የጉምሩክ ባለሥልጣን የሚከፍልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል አንድ እቃ በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ በሕጉ መሠረት የተከፈለ ኪራይ አይመለስም፡፡

የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕጉ መሠረት የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተሟልቶ ላልተፈፀመበት እቃ ዲክላራሲዮን ለመስጠት አይገደድም፡፡

የጉምሩክ ባለሥልጣን የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተሟልቶ ላልተፈፀመበት እቃ ዲክላራሲዮን ባለመስጠቱ ምክንያት በሕግ የሚጠየቀው ኪሣራ የለም፡፡

በዚህ ጉዳይ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ በሕጉ መሠረት የተከፈለውን ኪራይ የጉምሩክ ባለሥልጣን ለአሁኑ ተጠሪ እንዲመለስለት፣ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተሟልቶ ላልተፈፀመበት እቃ ዲክላራሲዮን እንዲሰጥ ዲክላራሲዮን ባለመስጠቱ ምክንያት የተጠየቀውን ኪሣራ እንዲከፍል በሚል በተሰጠው ውሣኔም የሕግ ስህተት ተፈጽሟል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንን ጉዳይ በማስመልከት በፍ/መ/ቁ.3417፣ በ14/10/96 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔም ሆነ ጉዳዩራ በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 32978፣ በ16/2/97 ዓ.ም. ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በሚል የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

ጉዳዩ ስለተወሰነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡